

ትምህርት 6 ለነሐሴ 2፣
2018

# የመንፈስ ስጦታዎች


“ፍቅርን ተከታተሉ፥ መንፈሳዊ
ስጦታንም ይልቁንም ትንቢት መናገርን
በብርቱ ፈልጉ።”
(1 ቆሮንቶስ 14:1)

የቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን በበርካታ ጉዳዮች የተከፋፈለች እንደነበረች ግልጽ ነው። በሰባኪዎች ጉዳይ፣ በአመጋገብ ጉዳይ፣ ስለማግባትና አለማግባት ጉዳይ እናም በመንፈስ ስጦታዎች ጉዳይ ከእነርሱ ውስጥ የሚበልጠው ማንኛው እንደሆነ አይስማሙም ነበር።



ጳውሎስ ቀድመው ለተነሱት ችግሮች መፍትሄ ከሰጠ በኋላ መንፈሳዊ ስጦታዎችን በተመለከተ የችግር መንስኤ ሳይሆኑ የአንድነት መንስኤ መሆናቸውን ለማሳየት ሲጥር ነበር (1ቆሮ 12-14)።

ከሁሉም የሚበልጠው ስጦታ የቱ ነው? የቱም አይበልጥም! ለምን?



**መንፈሳዊ ስጦታዎች:**

- ብዙ ስጦታዎች፣ አንድ ሰጪ
- ብዙ አባላት፣ አንድ አካል

**የአንድነት ቁልፍ:**

- የፍቅር ቁንጮነት

**የተለዩ ስጦታዎች:**


- የልሳን ስጦታ
- የትንቢት ስጦታ

# መንፈሳዊ ስጦታዎች



# ብዙ ስጦታዎች፣ አንድ ሰጪ

“የጸጋም ስጦታ ልዩ ልዩ ነው መንፈስ ግን አንድ ነው፤” (1 ቆሮንቶስ 12:4)



**መንፈሳዊ ስጦታዎችን የሚሰጠው ማን ነው? (1ቆሮ 12:4-6)**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1ቆሮ 12:4 | | ስጦታዎች | | አንድ መንፈስ |
| 1ቆሮ 12:5 | ልዩ ልዩ | አገልግሎቶች | አሉ ነገር ግን | አንድ ጌታ አለ። |
| 1ቆሮ 12:6 | | ስራዎች | | አንድ እግዚአብሔር |

መንፈሳዊ ስጦታዎች

ሰጪው

በመንፈሳዊ ስጦታዎችና በሰጪው መካከል ያለውን ግንኙነት መረዳት እንድንችል ጳውሎስ ብዝሃነታቸውን በሚገልጹ ሶስት ቃላት አስቀምጦልናል: እነዚህም ስጦታዎች፣ አገልግሎቶች እና ስራዎች የሚሉ ናቸው።



ነገር ግን ሰጪው መንፈስ ቅዱስ፣ ጌታ ኢየሱስ እና እግዚአብሔር አብ አንድ ነው። ይህም ማለት ሥላሴ በጋራ ይሰራሉ ማለት ነው (ዮሐ 14:16)።





እግዚአብሔር ግን ስጦታን የሚሰጠው እንደ ግሪክና ሮማ “አማልክት” አይደለም (1ቆሮ 12:2)። ከስጦታው ጋር የሚመጣ ሐሴት ወይም ስጦታውን ለጥቂቶች ብቻ ለይቶ የመስጠት ነገር የለም (ለምሳሌ እንደ ጠንቋዮች)።

# ብዙ ስጦታዎች፣ አንድ ሰጪ

"የጸጋም ስጦታ ልዩ ልዩ ነው መንፈስ ግን አንድ ነው፤" (1 ቆሮንቶስ 12:4)

እግዚአብሔር ለተለያዩ ሰዎች የተለያዩ ስጦታዎችን የሚሰጠው ለምንድን ነው? (1ቆሮ 12:7)

መንፈሳዊ ስጦታዎች የሚውሉት ለቤተክርስቲያን "ጥቅም" ነው። አንድን ዓላማ ለማሳካት ስጦታውን ለየትኛው ሰው መስጠት እንዳለበት የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው።



ጳውሎስ ከታወቁት ስጦታዎች መካከል እንደ ምሳሌ የጠቀሳቸው የትኞቹን ነው? (1ቆሮ 12:8-10፣ ሮሜ 12:6-8፣ ኤፌ 4:11-12)

| 1 ቆሮንቶስ 12:8-10 | ሮሜ 12:6-8 | ኤፌሶን 4:11-12 |
|---|---|---|
| ጥበብን መናገር | አገልግሎት | ሐዋርያነት |
| እውቀትን መናገር | ማስተማር | ወንጌል ሰባኪነት |
| እምነት | መምከር | እረኝነትና አስተማሪነት |
| የመፈወስ ስጦታ | በልግስና መስጠት | |
| ተአምራትን ማድረግ | ማስተዳደር | |
| ትንቢት | ምህረት ማድረግ | |
| መናፍስትን መለየት | | |
| በልሳን መናገር | | |
| ልሳንን መተርጎም | | |

# ብዙ አባላት፣ አንድ አካል

**"አካልም አንድ እንደ ሆነ ብዙም ብልቶች እንዳሉበት ነገር ግን የአካል ብልቶች ሁሉ ብዙዎች ሳሉ አንድ አካል እንደ ሆኑ፥ ክርስቶስ ደግሞ እንዲሁ ነው፤" (1 ቆሮንቶስ 12:12)**



እግዚአብሔር አንድ ነው ነገር ግን እያንዳንዱ የሥላሴ አካል የራሱ ተግባር አለው። እንደዚሁም ቤተክርስቲያን አንድ ነች ነገር ግን በምድር ላይ ያለች የክርስቶስ አካል እንደመሆኗ በውስጧ ያሉ እያንዳንዱ አካላት የራሳቸው ተግባር አላቸው (1ቆሮ 12:12-13)።

ጳውሎስ የሰውን አካል እንደ ምሳሌ በመጠቀም በልዩነት ውስጥ ያለውን አንድነት አሳይቶ ነበር። አይን የማየት "ስጦታ" አለው ነገር ግን ጆሮ ይህን አይችልም። ነገር ግን ሁለቱ በጋራ በመስራት ይተባበራሉ። በተመሳሳይ በቤተክርስቲያን ውስጥ እያንዳንዱ ሰው በተቀበለው ስጦታ መሰረት የራሱ ሚና አለው (1 ቆሮ 12:28-30)።





ሁሉም ሰው አስፈላጊ እንደሆነ እዚህ ጋር እንመለከታለን፤ እንዲሁም ማንም ከማንም እንደማይበልጥ፣ ሁሉም ሰው ስለ ሌላው አካል ግድ ሊለው እንደሚገባ፣ እና ሁሉም ሰው ለቤተክርስቲያን አንድነት መስራት እንዳለበት እናያለን (1ቆሮ 12:15-27)።



# የአንድነት ቁልፍ



# የፍቅር ቁንጮነት

"ነገር ግን የሚበልጠውን የጸጋ ስጦታ በብርቱ ፈልጉ። ደግሞም ከሁሉ የሚበልጥ መንገድ አሳያችኋለሁ።"
(1 ቆሮንቶስ 12:31)



ፍቅር "ከሁሉ የሚበልጠው የጸጋ ስጦታ" ነው (1 ቆሮ 12:31)። በአማኝ ሕይወት ውስጥ የሚፈራ የመንፈስ ፍሬ ነው (ገላ 5:22)። መንፈሳዊ ስጦታዎች በአግባቡ ጥቅም ላይ የሚውሉት በፍቅር በኩል ነው።

የልሳን ስጦታ ያለ ፍቅር "እንደሚጮኽ ናስ ወይም እንደሚንሸዋሸው ጽናጽል " ነው። የትንቢት ስጦታ፣ የእውቀት ቃል ስጦታ እና የእምነት ስጦታ ያለ ፍቅር ትርጉም የላቸውም። የቸርነት ስጦታ እና ራስን ለሞት የመስጠት ጸጋ ያለ ፍቅር ከንቱ ነው (1ቆሮ 13:1-3)።

በ1ኛ ቆሮንቶስ 13:4-7 የመንፈስ ስጦታዎችን በመለማመድ ውስጥ እንዴት ልንመላለስ እንደሚገባ መመሪያ ተቀምጦልናል :

**የፍቅር ተግባር የሆነው**

- ይታገሳል
- ቸርነት ያደርጋል
- በእውነት ይደሰታል
- ይቅር ይላል
- ሁሉን ያምናል
- ሁሉን ተስፋ ያደርጋል
- በሁሉ ይጸናል

**የፍቅር ተግባር ያልሆነው**


- አይቀናም
- አይታበይም
- አይመካም
- የማይገባውን አያደርግም
- የራሱን አይፈልግም
- አይበሳጭም
- በደልን አይቆጥርም
- በአመጽ ደስ አይለውም

# የተለዩ ስጦታዎች



# የልሳን ስጦታ

“ስለዚህ በልሳን የሚናገር እንዲተረጉም ይጸልይ።” (1 ቆሮንቶስ 14:13)



ጳውሎስ ስለልሳን ስጦታና ስጦታውን በአግባቡ ስለመጠቀም የሰጠው ትኩረት የሚያሳየን አንዳንድ የቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን አባላት ስጦታውን ያለአግባብ ሲጠቀሙት እንደነበርና ይህንም ተከትሎ በጉባኤው አምልኮ ውስጥ ረብሻና ግራ መጋባት መፈጠሩን ነው (1ቆሮ 14:23)።

የልሳን ስጦታ ተናጋሪው በማያውቀው የሰው ወይም የመላዕክት ቋንቋ የመናገር ችሎታ ነው (1ቆሮ 13:1)። ይህን ቋንቋ አድማጮች የማያውቁት ከሆነ ሊተረጎም ይገባል (የሐዋ 2:8፣ 1ቆሮ 14:2፣ 13-14፣ 27-28)።

ጳውሎስ ሰዎቹ በሙሉ በልሳን መናገር ቢችሉ ደስ እንደሚለው የተናገረውን አንዳንዶች በተሳሳተ መንገድ ተርጉመው ሁሉም ይህን ስጦታ ሊቀበሉ ይገባል ብለው ያስባሉ (1ቆሮ 14:5)።



እውነታው ግን ይህ ምኞቱ ለሁሉም ስጦታዎች የተናገረው መሆኑ ነው (1ቆሮ 14:1)። ጳውሎስ “መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ሰው የሚሰጠው ለጋራ ጥቅም” መሆኑን አስቀድሞ በግልጽ አስቀምጦአል(1ቆሮ 12:7)። ሁሉም ሰው ተመሳሳይ ስጦታን የማይቀበለው ለዚህ ነው።

# የትንቢት ስጦታ


“ትንቢትን የሚናገር ግን ለማነጽና ለመምከር ለማጽናናትም ለሰው ይናገራል።” (1 ቆሮንቶስ 14:3)



የትንቢትን ስጦታ የወደፊት ክስተቶችን በማወቅ ላይ ብቻ ልንወስነው አይገባም። የትንቢት ቀዳሚ ጥቅሙ ለማነጽ፣ ለመምከርና ለማጽናናት ነው (1ቆሮ 14:3)።

ጳውሎስ ለዚህ ስጦታ ከሁሉም በላይ ትኩረት ይሰጣል (1ቆሮ 14:1፣ 4፣ 22-25)። ነገር ግን በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋል እንዳለበትና ግራ መጋባትን መፍጠር እንደሌለበት ያሳስባል: “ነገር ግን ሁሉ በአገባብና በሥርዓት ይሁን።” (1ቆሮ 14:40፣ ተመ 1ቆሮ 14:29-33)።





የቅሬታዋ ቤተክርስቲያን ከልዩ ማንነቷ አንዱ የትንቢት ስጦታ በኤለን ጂ ኋዋይት ህይወትና ስራዎች ውስጥ መገለጡ ነው (ራዕይ 12:17፣ 19:10)። ነገር ግን እውነተኛ ነቢይን የምንለየው እንዴት ነው?



ነቢዩ የተናገረው የወደፊት ክስተት ሊፈጸም ይገባል (ዘዳ 18:22፣ ኤር 28:8-9፣ ዮና 4:2)



የነቢዩ መልዕክት ከቀደሙት ነቢያት ጋር መስማማት አለበት (ዘዳ 13:1-3፣ኢሳ 8:20)



ኢየሱስ ሥጋ ለብሶ መገለጡን መመስከር አለበት (1 ዮሐ 4:1-3)



ህይወቱ ከሚሰብከው መልዕክት ጋር መስማማት አለበት (ማቴ 7:15-20)

“ጌታ ካዘጋጀው ነገር ሁሉ ለወንዶችና ሴቶች ልጆቹ ልዩ ልዩ ስጦታዎችን ለመስጠት ከማሰቡ በላይ ውብ የሆነ ነገር የለም። ቤተክርስቲያን ለጌታ በልዩ ልዩ ዛፎች፣ እጽዋትና አበቦች የተዋበች የአትክልት ስፍራው ነች። የሂሶጱን ተክል የዝግባን አቋም ይኖረዋል ብሎ አይጠብቅም፣ የወይራውንም ዛፍ ዘለግ ካለው ከዘንባባ ቁመት እንዲደርስ ግድ አይለውም። ብዙዎች ውሱን የሆነ የኃይማኖትና የአዕምሮ ስልጠና ብቻ ቢኖራቸውም በጌታ እየታመኑ በትህትና ቢተጉ እግዚአብሔር ለእነርሱ ያዘጋጀው ስራ አላቸው...”

ሰራተኞቹ አንዱ ለሌላው እንደሚያስፈልገው ይረዱ ዘንድ ልዩ ልዩ ስጦታዎች ለተለያዩ ሰዎች ተበርክተዋል። እነዚህንም ስጦታዎች የሚሰጠው እግዚአብሔር ነው፣ የሚውሉትም ለእርሱ አገልግሎት እንጂ ስጦታ ተቀባዩን ከፍ ለማድረግ ወይም ሰውን ከፍ ለማድረግ አይደለም ነገር ግን የዓለም ቤዛን ከፍ ለማድረግ ነው። እውነቱን በመወከል ለሰው ዘር ሁሉ ጥቅም የሚውሉ ናቸው እንጂ ሀሰትን ለመመስከር አይደለም።

EGW (Ye Shall Receive Power, July 1)